# ይድረስ ለሊቅ ተክሌ የሻው የሞረሽ ወገኔ ማኅበር ሊቀ መንበር

በተቀዳሚ የተከበረ ሰላምታችን ይድረስዎ።

ዛሬ ይህን ጦማር ልንጽፍልዎ ያነሳሳን ዐቢይ ጉዳይ ሰሞኑን ዶክትር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ በኢሳት ቴሌቭዥን ቀርቦ ከጋዜጠኛ ፋሲል የኔዓለም ጋራ የኢትዮጵያን ታሪክ አስመልክቶ የዘባረቃውን፣ በተለይም ፀረ ዐማራ ጥላቻ ቅስቀሳ ማናፈሱን በሚመለከት ረገድ እርስዎ በቅጽበት የተነዛውን ውሸትና የፈጠራ ታሪክ በመቃወም ከሆድ አደሩ ጋዜጠኛ ጋራ ከፍተኛ ግብግብ ገጥመው ለሰጡት ትክክለኛ ምላሽና ጥልቅ ግንዛቤ ክፍተኛ ምስጋና እንዲሁም ታላቅ አክብሮታችንን በትህትና እንቃርባለን። ፕሮፌስር ጌታቸው ኃይሌ.ም ወዲያው የሰጡት ምላሽ ትክክለኛ ተገቢ ሆኖ አመስግነናል። በመቀጠልም ተጨማሪ ታሪካዊ ማስረጃዎችንና አስፈላጊ ሆነው የተመለከትናቸውን እንሆ ቀጥሎ በዝርዝር አክለናል።

**፩ኛ.** የኢሳት ጋዜጠኛ ተብዬው ፋሲል የኔዓለም የፀረ ዐማሮች አፈ ቀላጤ መሆኑን በግልጽና በተደጋጋሚ ማሳየቱን አሳይቷል። እንደሱ ያሉትስ ቅምጥል ሆዳም ዐማራ ተብዬ ልሂቃን ሁሉ በምቾት ሶፋ ወንበር ላይ ተወዝፈው ፀጉር የሚሰነጥቁ ተራቢዎች፣ ከላም አለኝ በሰማይ ጥቁር ወተት የሚያልቡት ሌሊቱ የነጋብት ዥብና የታሪክ አተላ ናቸው።

**፪ኛ.** ዶክተር ላጵሶ ድሌቦ የተባለው ምሁር እስስት ነው። በመጀመሪያ ሃይማኖቱን እስልምናን ቀይሮ የሱዳን ኢንቲሪየር ሚሲዮን ፍርፋሪ ለቃሚና ምልምል እንደሆነ አሳውቆናል። ለከፍተኛ ትምህርት አሜሪካን ሄዶ ከተመለሰ በኋላ በዘመነ ደርግ አብዩተኛ ነኝ ብሎ <u>የኢትዮጵያ የረጅም የሕዝብና መንግሥት ታሪክ</u> በሚል ርዕስ ለጻፈው ታላቅ ዕውቅናና አክብሮት ተሰጥቶት፤ እንዲሁም የብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት የተሰኘው ድርጅት ዋና ተዋናይ ሆኖ ከቆዩ በኋላ ከሰኔ ወር 1983 ዓ.ም ጀምሮ ኮቱን ገልብጠና የስልፋን አቅጣጭያ አስተካክሎ የወያኔ ትግሬ ሕወሐት የጎሣ አደረጃጀትና የክልል ሸንሸና አቃላጭና አማካሪ በመሆን ዛሬ በኢትዮጵያ ምደር ለሰፈነው የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ አጋፋሪ ሆኗል። የጎሣ ፌደራሊዝም የተሰኘው የኢትዮጵያን ሕዝብ ልክ እንደ ፋሽስት ጣሊያን የአምስት ዓመታት ወረራው ወቅት በቋንቋ መለያ ተሸንሽኖ ክልል በተባለው የጎሣ እሥር ቤት እየታመሰ ሩብ ምዕተ ዓመት አስቆጥሯል። በተለይም ዐማራውን ሕዝብ ለይቶ በዋና ጠላትነት በመፈረጅ የዘር ማጥፋትና ማፅዳት ዘመቻ ሰለባ ሆኗል። ለም መሬቱን ከሰሜን በጌምድር ወገራ አውራጃ ወልቃይት ጠገዴን፣ ከወሎ ራያና ቆቦን፣ ከጎጃም መተከል አውራጃን፣ ከሸዋ ደራ ኮራ መራቤቴን፣ ግንደበረትን፣ ሰላሌ ግራርያ ደብረ ሊባኖስን፣ ተጉለት ወግዳን፣ መናገሻን፣ የረርን ወዘተረፈ ያለ አግባብ ተክልለውብታል።

ከሁሉም በላይ ታሪክ ለማያውቀው የፈጠራ ክልል ኦሮሚያ ተብይው ያለ ነባሩ ያማራ ሕዝብ ፈቅድና ስምምነት ወያኔ / ሻዕቢያ ትግሬዎችና ኦነግ በምዕራባውያን ርዳታ ድጋፍ ተቀራምተዋል። በኦሮሚያ ክልል ተብዬው ውስጥ የሚኖሩ በብዙ ሚሊዎን የሚቆጠሩት ዐማሮች ሰባዊ መብታቸው ተረግጦ በቋንቋቸው ዐማርኛና በራሳቸው ፊደል እንዳይጠቀሙና እንዳይማሩ ተከልክለው ጥቁር ፈረንጅ ሆነዋል። ቁቤ ላቲን ፊደልን በግዳጅ እንዲጠቅሙ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ተገደዋል። ከዚህ ሌላ ያማራ ገበሬዎች ከትውልድ ቀያቸውና መኖሪያ ቤታቸው በኦህዴድ ቅጥረኛ ካድሬዎች ቅስቀሳ ሃብት ንብረታቸውን እየተቀሙ ተገድለዋል ተፈናቅለዋል። ለምሳሌ ከሸዋ ክፍለ ሀገር በቅርቡ እንኳን የሆነውን መጥቀሱ ሁኔታው በግልጽ ያሳያል። የምዕራብ ሺዋ ዞን ተብዬው የጅባትና ሜጭያና መናገሻ አውራጃዎች ውስጥ የኖኖ ወረዳ ፓሊስ አዛዥ ኢንስፔክተር ኃይሉ ድሪባ፣ የኖኖ አሉ ቀበሌ ሊቀ መንበር አቶ ጎሣዬ ገቹና የመቶ አለቃ ገነነ በየነ የተባሉት የፖሊስ አባላትና የቀበሌው ባለሥልጣናት አስተባባሪነት ያካባቢው ወረሞ የዐማራውን ነባር ነዋሪ ለይተው እንዲያጠቃ በአድረጉት የጥላቻ ቅስቀሳ ዘመቻ ሚያዚያ ዘጠኝ ቀን 2007 ዓ.ም 85 ገበሬ አባወራዎች እንበለ ፍትሕ ለእሥራት ተደርገዋል። በማግስቱም ሚያዚያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም ከቀኑ በሦስት ሰዓት ላይ ያማራዎች መኖሪያ ቤት ንብረት እየተመረጡ ተቃጥለዋል። እነዚህ ባለሥልጣናት አቅደውና ተዘጋጅተው በቀሰቀሱትና በፈጠሩት ሁክት ያንድ ሰው ሕይወት ወዲያው ሲያልፍ ከ10 በላይ የሆኑትም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በቀበሌው 99 የሳር ክዳን ቤቶችና 25 የቆርቆሮ ክዳን የነበራቸው ቤቶች፣ የእህል ጎተራዎች፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁና መሣሪያዎች ጋይተዋል። በቃጠሉው ከፍተኛ ሃብትና ንብረት ከመውደሙ ሌላ በተቀሰቀሰው የጎሣ ማጽዳት ዘመቻ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሴቶች፣ ሕፃናትና አዛውንቶች ከትውልድ ቀያቸው ተፈናቅለው ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሲሉ ወደ አጎራባቹ የጉራጌ ሀበሽጌ ወረዳ ወገናቸው ዘንድ በመሰደድ ርዳታና የመጠለያ እንክብካቤ ማግኘታቸውን የኢትዩጵያ ሰብአዊ መብት ጉባዔ 136ኛው ልዩ መግለጭያ ያረጋግጣል።

ይህን ዓይነቱ የተቀነባበረ የጎሣ ማጽዳት ቅስቀሳና ወንጀል የሚፈጸመው በኖኖ አሉ ቀበሌ ብቻም ሳይሆን በሺዋ ክፍለ ሀገር ውስጥ በሰሜን ሺዋ ዞን ተብዬው በደራ ወረዳ፣ በደብረ ሊባኖስ፣ በግራር፣ በያያ ጉለሌ፣ በቅምብቢት ወዘተ ወረዳዎች እንዲሁም በምሥራቅ ሺዋ ዞን ተብዬው በፈንታሌ፣ በቦሰት፣ በናዝሬት፣ በሊበን/ዝቋላ፣ በዝዋይ፣ በግምቢቹ ወረዳዎች፤ በምዕራብ ሺዋ ዞን ተብዬው ውስጥ በግንደበረት፣ በአምቦ፣ በጅባት፣ በአዳ በርጋ፣ በሆለታ፣ በወልመራ፣ በጀልዱ፣ ወዘተረፈ ወረዳዎችና ቀበሌዎች በኦሕዴድ ታጣቂ ባለሥልጣናት ቀስቃሽነት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት ዘወትር በነባር የሺዋ ተወላጆች ላይ ተፈጽሟል፤ ይፈጸማል።

ሌላው አረመኔያዊ ድርጊት በጎጃም መተከል አውራጃ ውስጥ ዐማሮች በጉምዝ የወያኔ ትግሬ ታጣቂ አረመኔዎች እንደ የዱር አራዊት ታድነው መበላታቸው ነው። ዐማራውን ማኅበረሰብ ለይቶ ከያለበት የማፈናቀሉና የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ መንዛቱ በሰፋትና ያለማቋረጥው በመካሄድ ላይ ነው። ስለሆነም ላጽሶ ድሌቦ አባሪ ተባባሪ በምሆን

የወረሞ ወይም የጋላ ጎሣ ነፃ አውጭና ተወካይ ነንባይ የአነግ፣ የወያኔ ትግሬ ተለጣፊ አገልጋይ ኦህዴድና ሌሎች ቡድኖችና ግለሰቦች ዘወትር የሚነዙትን ፀረ ዐማራ ፕሮፓጋንዳ በኢሳት ቴሌቪዥን ቃለ መጠይቁ ላይ፤

<<የኢትዮጵያ ታሪክ የዐማሮች ተረት ነው፤ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ደብተራዎች የጻፉት ተረት ነው፣ የነገሥታት ታሪክ ነው......>> እያለ እንበለ እፍረት ለከትና መጠኑን አልፎ ሲያናፋ ተሰምቷል። እረ ለመሆኑ ነገሥታቱ ያለሕዝብ፣ ያለ አገር በሰማይ ኅዋ ላይ ነበረ እንዴ የሚኖሩት? ፕሮፌሰር አሊ ማዙሪ (ነፍሳቸው ትማር) የጥገኝነት ገዳይ በሽታ በአፍሪቃውያን ምሁራን ዘንድ መስፋፋቱን ሲገልጹት የአፍሪቃ ጦጣ " cultural apes" ምሁራን ማለትም ከምዕራቡ ዓለም ያዩትና የሰሙትን እንዳለ ገልባጮች እንጂ ነፃ አሳቢዎችና ሐቀኛ ተመራማሪዎች ያለመሆናቸውን ለመጠቆም ነው።

በኢትዮጵያ ጥንታዊ አገር ረጅም ታሪክ ውስጥ ሦስት ነገሮች ወሳኝነት ነበራቸው። እነዚህም ቤተ መንግሥት፣ ቤተ ክህነትና ሕዝብ ናቸው። ቤተ መንግሥት ነጋሢ፣ ቤተ ክህነት፣ አንጋሽና አወዳሽ፣ ሕዝብ አንጋሽ ሆኖ ዕድር እያደረገ ነው የኖረው። ዕድር ለንጉሥ ያስቸግር የሚባለውና ንጉሥ ሲሞትና አዲስ ሲሰየም የሞትንም እኛ ያለንም እኛ ተብሎ አዋጅ የሚነገረው የሦስቱን ነገሮች መስተጋበር ለመግለጽ ነው።

የኛ ነገሥታት ዜና መዋዕል ሆነ ሥርዓተ መንግሥት በሚገባ በቋንቋችን ተመዝግቦ ቆየቶልናል። ኢትዮጵያዊ ያልሆናችሁና በኢትዮጵያ ጥንታዊ አገርነት የማታምኑት ሁሉ በኛ ታሪክ፣ ባሕል፣ ሃይማኖትና ኢትዮጵያዊነት ላይ አትሞጣሞጡ።

ውሻ በበላበት ይጮኽል እንዲሉ ላጵሶ ከሥር መሠረቱ የሚሲዩናውን ፍርፋሪ ለቃሚ፣ የወታደራዊ ደርግ ካድሬና ዛሬ ደግሞ የወያኔ ትግሬ ቅጥረኛ ሎሌ በመሆኑ ከቶ ማን ይገረማል! ዶክተር ላጵሶ ቀደም ብሎ የጻፈውን ሁሉ ክዶል። የጋላን ነገድ የ16ኛው ክፍለ ዘመን ወረራና መስፋፋት ሽፍጦ የፈጠራ ልብ ወልድ ያነበንባል።

የጋለ ሉባ ወራሪ በየስምንት ዓመቱ ተከታታይ የሽምቅ ውጊያ ስለምን ድል ቀንቶት በኢትዮጵያ ለም መሬት ከደቡብ ምሥራቅ ባሌ ኬኒያ ጠረፍ ማዶ በብናድርና ቦረና ጥንታዊ አገሩ ተነስቶ በስተሰሜን እስከ ትግሬ፣ ከምሥራቅ ዘይላ በርበራ እስከ ምዕራብ ዳሞትና ቢዛንሞ (ወለጋ)፣ እስከ እናሪያ ድረስ የሜጭያ ቱላማ ጎሣዎች ተንሰራፍተው መስፈራቸውን ስለምን ዛሬ ይሸፈጣል?

የጋላ ጎሣዎች በአገራችን ቋሚ ሰፋሪ ለመሆን የበቁት የኢትዮጵያ አጤ መንግሥትና ሕዝብ

ከኦቶማን ቱርክና አረብ ቅጥረኛ ከነበረው ግራኝ አሕመድ ጋራ ለ14 ዓመት በተካሄደው ጅሃዳዊ ወረራ፣ ከፍተኛ የሕዝብ እልቂትና የባሕል ውድመት መድረሱ ወሳኝ ምክንያት እንደሆነ የተረጋገጠ ሐቀ ነው። ታዲያ! የጋላ ወይም ወረሞ ዘላን ጎሣዎች ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ በኦሮሚያ ክልል ተብዬው ነባር ሕዝብ እንደሆኑ አስመስሎ መወሻከት ምን ይሉታል? ወራሪውና መጤ ሠፋሪውስ ማነው? በማንስ አገር የማን ኦሮሚያ ሪፑብሊክ የመሰረታል? የኦሮሞን ሕዝብ እወክላለሁ የሚለው ኦነግ የሚለፍፈው በሬው ላም ወለድ በኢትዩጵያ ውስጥ የኦሮሞ ሕዝብ ሰፍሮበት የሚገኘው አካባቢ ሁሉ ከሥር መሠረቱ የኦሮሞ ክልል እንደሆነ አስመስሎ ከማናፈስ ሌላ "አጤ ምኒልክ የዛሬ አንድ መቶ ዓመት ገደማ በመውረር በቅኝ ግዛትነት ሰለተያዘበት በአውሮፓ ቅኝገዥዎች አገዛዝ ሥር እንደሚገኝ ሕዝብና አካባቢ የኦሮሞ ሕዝብ የሰፈረበትን አካባቢ ከኢትዩጵያ ገንጥሎ ነፃ በመውጣት ራሱን የቻለ መንግሥት ማቋቋም አለበት በማለት ኦነግ ከኢትዩጵያ የቆዳ ስፋት ሦስት አራተኛ የሚሆነውን በመከለል ኦሮሚያ የሚል ሰያሜ ሰጥቶት አዲስ ነፃ ሀገር በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ለመመሥረት በማሰብ ኦሮሞ ያልሆኑትን ዐማሮች ከተጠቀሰው ክልል ውስጥ በዘር ማጥፋትና ማጽዳት ዘመቻና በኃይል ማስፈራራት አባሮ ዓላማውን ለማሳከት ደፋ ቀና በማለት ላይ ነው።

የዓለም ጥቁር ሕዝብ ዘርያ አለኝታና ኩራት የሆኑት ታላቁን የኢትዩጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ያውሮፓ ዘረኛ ቅኝገዥዎችንና ተስፋፊዎችን ቅስም የሰበሩትን፣ ከማዕከላዊው መንግሥት በወረሞ ወረራ ምክንያት ተነጥለው የቆዩትን የደቡብ ኢትዩጵያ ነባር ሕዝብን ከአካባቢው ባሪያ ፈንጋይ የወረሞ አባቆሮችና አክፋላ ነጋዴዎች ነፃ ያወጡትን መሪና ያማራውን ሕዝብ ለይተው የቅርብና የሩቅ ጠላቶቻችን ዘወትር የሚያላዝኑት የውሸት ክምር "የኦሮሚያን የገዳ ሪፑብሊክ አበሻዎች በአውሮፓውያን ኢምሪያሊስቶች ርዳት ቅኝ ግዛት አድርገዋል" እያሉ ይለፈፋል።

**፫ኛ.** ላጽሶ የጥንት ኢትዩጵያ አክሱም ግዛት ከትግሬና ከኤርትራ ክፍለ ሀገራት አያልፍም እያለ የዋሸው የወያኔ ትግሬ የሃማሴን ባንዳ ውላጅ ስብሐት ነጋ ያነበነበውን በማስተጋባት ብቻ ነው። ያክሱም ግዛትማ በሰሜን እስከ ግብፅ ጠረፍ ኑቡያን ሲያጠቃልል፤ በስተምሥራቅ በርበራ፣ ዘይላን፣ በምዕራብ ጋምቤላን ጨምሮ እስከ ነጭ አባይ ወንዝ ይደርሳል፤ በስተደቡብ እስከ ታንዛኒያ ካማውያን ነዋሪዎችን ሲይዝ፣ ከቀይ ባሕር ማዶ ደግሞ ደቡብ የመንን ያጠቃልል እንደነበር ያታወቃል።

**፬ኛ.** ሰለ ዐማራ ሕዝብ ፍጹም የተሳሳተ ትረካው በጥላቻና በዝቅተኛነት ሴሜት ታውሮ ሲለፍፍ ተደምጧል። የአክሱም የኢትዮጵያ መንግሥት ከ፯ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በአረቢያ ባሕረ ሰላጤ ምድር የእስልምና ሃይማኖትና ካሊፋት ሲመሠረትና ሲስፋፋ አክሱም የቀይ ባሕር ንግድ መሥመርን የመቆጣጠር ኃይሉ ቀስ በቀስ እየተዳከመ ሂዷል። ከዚህም ሌላ ገባሩ የነበሩት ልዩ ልዩ የቤጃ ጎሣዎች ተባብረው ስለወረሩት መዲና አክሱምን ለቆ በስተደቡብ አቅጣጭያ ወደ ላስታና ሸዋ ተዛውሯል። ዩዲት ጉዲት ደግሞ ያክሱምን ነገሥታትና መኳንንት ለ40 ዓመታታ ያህል ማሳደዷ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል።

የዛጉዌ ነገሥታት ከላስታ መዲናቸው መላውን አገር እስከ ባሌ፣ ደዋሮ፣ ወጅ፣ ጉራጌ፣ ከምባታ፣ ወላሞ፣ ሸዋ፣ ዳሞት፣ ሲገዙ ቆይተዋል። ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀመሮ እስከ ጋላ ወረራ 16ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ታላላቅ የኢትዩጵያ ነገሥታት በየረርና በእንጦጦ፤ በእንድግብጣን መናገሻ አውራጃ፣ በተጉለት ወዘተረፈ አብዛኛውን ጊዜ ሲኖሩ አቢያተ ክርስቲያን ተክለዋል፣ ገዳም ገድመዋል። አጤ ገላውዲዋስ በዝዋይ ወጂ ቋሚ ከተማ ለመሥራት አቅደው እንደነበረ በወቅቱ የነበሩት የፖርቱጋል ሰዎች ዓይን ምስክር ናቸው።

ከዛጉዊ ሥርዎ መንግሥት በኋላ ከአጤ ይኩኖ አምላክ ጀምሮ የኢትዩጵያ መንግሥት ማዕከል ወደ ሸዋ መዛወርን ብቻ በመጥቀስ ያማራ ሕዝብና ዐማርኛ መነገር ተጀመረ ማለት ነጭ ውሸት ነው።

ያማራ ሕዝብማ በአባይ ሸለቆና በኢትዩጵያ ምድር ከቅድመ ታሪክ ጀምሮ የኖረና የሚኖር ነው። የአፍሮ እሲያ ቋንቋ ቤተሰብ ሴማዊው ዘርፍ ምንጭ የኢትዩጵያ ስምጥ ሸለቆ ነው። የግእዝ ቀዳሚ ቋንቋም ያማርኛ እኸት ነው። ታዲያ! ያማራ ሕዝብን እያሌ ሺህ ዘመናታ ታሪክ በስምንት መቶ ዓመታት ገድቦ ውሸት ማናፈስ አንድም ጥላቻ ሁለትም የዝቅተኝነት ስሜት ነፀብራቅ ቅጥረኛነት ነው።

ታሪክ የሌላችሁ በኛ ከአምስት ሺህ ዓመታት በላይ የጽሀፍ ታሪክና ሥልጣኔ እየቀናችሁ ባትጨናበሱ ይሻላል።

እንኳንስ የኛ በብርና፣ በድንጋይ ሰሌዳ የተጻፉት አያሌ ሰንዶችና የሥነ ቋንቋ ጥናት ማስረጃዎች ይቅርና ሥልጣኔየለሽ መደዴ ዘላኖች ተረት ተረትም እንኳ ለጽሑፍየለሽ

የቃል ተራኪ ማኅበረሰቦች ታሪክ መጻፊያነት ሰነድ ትንሽ ጥብታ ያበረክታል መባሉን ምነው አያ ላጵሶ ድሌቦ እንዳልሰማና እንደማያውቅ ሆኖ የኢትዮጵያ ዕውቅ ባለሙያ የቤተ ክርስቲያን ደብተራዎች እንደ አባ ባሕርይ፣ አለቃ ተክለየሱስ ዋቅጅራ፣ አባ ጊዎርጊስ፣ አባ ጽጌ ድንግል፣ አለቃ ዘነበ፣ አባ ጢኖ ወዘተረፈ የመሳሰሉት ያዘጋጁት ጽሕፋዊ ሰነድ ተረት ነው እያላ ያሞጠሙጣል።

ዶክተር ላጵሶ ድሌቦ በመጀመሪያ ግእዝ ተምረህ ተምንጬ ተረዳ፣ ተመራመረ። ፈረንጅ በአበሻ ጥላቻ ተርጉሞ የጻፈልህን ሳይገባሕ ተግተህ አታስካካ።

ለምሳሌ ስለ ክብረ ነገሥት የቀባጠርከው ፍጹም ቱሪማንቱሪ ነው። ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን በአጤ ካሌብ ዘመን እንደሆነ የተደረጉት ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ዋና ምንጬም ብሉይና ሐዲስ ኪዳን ናቸው። መጽሕፍ ቅዱስ ደግሞ ተረት አይደለም።

፳፯. ሊቅ ተክሌ የሻው አዲስ አበባን በተመለከተ የሰጡት ምላሽ ሸጋ ነው። ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ እንዲሉ የላጵሶ ነገር አብቅቶለታል። በባንቱስታን የጎሣ ፖለቲካ አቀንቃኝነቱን አዲስ አበባ የሸዋ ክፍለ ሀገርና የኢትየጵያ ዋና መዲና መሆኗን ዓይኑን በጨው አጥቦ "አዲስ አበባ የኦሮሞ ምድር ነው።" ብሏል። ይህ ሰው በእርግጥም ፈጽሞ ዝቅ ቋል ወይም ደግሞ የኦነግ የኦሮሚያ ነፃ ሪፑብሊክ ምሥረታ ተስፈኞችን ለማስደሰት አቅዶና ፈልጎ በጥሩንባ ነፊነት ያገለግላል። ከዘጠኝ ሚሊዎን በላይ የሚሆኑትን የአዲስ አበባ ነዋሪዎቿን ዴሞክራሲያዊ መብትና ነፃነትን በግልጽ ተቃውሞ ከወረሞ ጠባብ ጎሠኞች ጋራ ተሰልፏል። እስቲ እንተያያለን።

ኦነግ ተብዬው አዲስ የፈጠራ ታሪክ በመንፈሳዊ አባቶቹ የአውሮፓ ፀረ ኢትዮጵያ፣ ፀረ ዐማራና ፀረ ኦርቶዶክስ አቀንቃኞች ልብወለድ የጎሣ ጥናት ተብሎ ተዘጋጅቶለታል። ኦነግ በነደፈው እቅድና ዓላማ መሠረት የአዲስ አበባ ነዋሪ ዐማራዎች መተላለፊያ መንግደ ተዘጋጅቶላቸው ከአባይ ማዶ ወደ ጎጃምና ጎንደር ይላካሉ በማለት ከአመራር አባል አንዱ የሆነው ታደስ ድባ በይፋ ተናግሯል። የኦሮም ተማሪዎች በአለፈው ዓመት የአዲስ አበባ ከተማ ዐቢይ ዕቅድ (Master plan) መስፋፋት ሃሳብ በመቃወም "ኦሮሚያ ለኦሮሞ ብቻ" ብለው በተለያዩ ከተሞች በሕይወትና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል።

በተለይም በአምቦ፣ በደምቢ ዶሎ፤ በባሌ ጎባ፣ በዓለም ማያ እንዲሁም በድሬዳዋ የሆነው የሚዘነጋ አይደለም።

አዲስ አበባ (እንዶጥና) በእቴጌ ጣይቱ ብጡል የተመሠረተችው በጥንታዊው ሽዋ ያማራ፣ የጋፉትና ጉራጌ ምድር ላይ ነው። በመሆኑም የቅርብ ዘመን ማለትም ከ1667 ዓ.ም ወዲህ መጤ ወራሪ ሰፋሪው ወረሞ በምድራችን ላይ ከሌላው ሕዝብ የበለጠ ልዩ የባለቤትነት መብት በጭራሽ የሌለው መሆኑ መታወቅ አለበት። አዲስ አበባ በሸዋ ምድር በአራቱም አቅጣጭያዎች ቢሻት አስከ ናዝሬት፣ እስከ ደብረ ብርሃን፣ እስከ ፍቼ፣ ወሊሶ፣ እስከ አምቦ፣ ወዘተረፈ መስፋትና ማደግ ተፈጥሯዊ ሐብቷ ነው። ማንም የወረሞ ጠባብ ጎሠኛና የወያኔ ኢሕአዴግ ቅጥረኛ አሸከር በአዲስ አበባ ሕዝብ ላይ አይፎልልም።

**፯ኛ.** ወያኔ ትግሬና ቅልብ ተለጣፊዎቹ በፀረ ኢትዩጵያዊነት ልክፍት ተመርዘዋል። በመሆኑም አዲስ የፈጠራ ታሪክ ለመጻፍ በዝግጅት ላይ ናቸው። የላጽሶ ሆያ ሆዬ የዚህ ዝግጅት አካል ነው። ዐማሮችን ከደቡብ ክልል ጉራፋርዳ ጨፍጭፎ በገፍ ያባረረውና ያፈናቀለው ሽፈራው ሽጉጤ የትምህርት ሚኒስቴርነት ተሾሞ አዲስ ታሪክ ፈልሳሚዎችን አሰባስቦ በአለፉት መንግሥታት በስንት ድካምና ጥረት ተገንብቶ የነበረውን የትምህርት ሚንስቴር መስሪያ ቤት ወደ ትልቅ የጎሣዎች ማድቤትነት ተቀይሮ ያገር በቀል ጎሠኞችና የባሕር ማዶ ፀረ ኢትዩጵያ አማካሪዎቻቸው ጥርቅም መፈንጭያ ሆኖ የኢትዩጵያ ትምህርት ጉዳይ አክትሞለታል።

ዐማራውን ሕዝብ ለይተው በቅኝ ገዥነት፣ የገዥ መደብ፣ ነፍጠኛ ተስፋፊ፣ ትምክህተኛ፣ ፊውዳል፣ ወዘተረፈ እያሉ ዛሬም በሥልጣን ወንበር ላይ ተደላድለው ቢፈናጠጡም እንኳን ባደረባቸው ስጋትና ፍርሃት እየባነኑ ጥላቻ ይነዛሉ። ፀረ ኢትዩጵያ ቅጥረኛ በመሆናቸው ነው ኢትዩጵያ የምትባል አገር ትናንት ከምኒልክ ወዲህ የተፈጠረች ናት እያሉ ሕዝቡ ከኢትዩጵያዊነት መንፈሳዊ ኩራትና ክብሩ ተዘናግቶ ርስ በርስ በጎሣ ግጭት እንዲጠመድ ባንዶች ያልፈነቀሉት ድንጋይና የማያደርጉት ሴራ ከቶ ምን አለ? ቢሆንም ምንም ጊዜ አይሳካላቸውም።

ኢትዩጵያ በልጆቿ መስዋትነት በነፃነቷ ፀንታ ለዘለዓልም ትኖራለች!

እነ፣

ዶክተር ገብሬ ጉልቱ፣ ዘብሔረ ሳይንት፣ ፕሮፌስር አዩ ሞሚና ዘብሔረ ወበራ ሐረርጌ ተፈረደኝ ኃይሌ፣ አባ ስግምግም ዘብሔረ ይፋት፣

ወይዘሮ የውብዳር ዘለቀ ዘብሔረ ዋድላ ደላንታ፤ ዶክተር ገለበው ሰንጎሳ ዘብሔረ ጋሞ